# በይ ብዕሬ

በይ ብዕሬ ምንላርግ አትበይ
ግጠሚ፤ አትች ተች
እኝኝ በይ ወትውች
ለማን ብለሽ ብእሬ
ካሰኘሽ ምላስ አውጭ
ምን ቸገረሽ ብእሬ
ተርቺ፤ ተርቢ አሽሟጭ
በይ ካለሽ
ልክ ልኩን ንገሪልኝ
ቀንድ ቀንዱን ስበሪልኝ
በይ ተዋጊ ብእሬ
ግጠሚ፤ አትቺ ተቺ
ተርቢ፤ አሽሟጪ ተርቺ
ብቻ!
ለእውነት ለፍትህ ሙቺ
አድር ባይ አተላን አጋልጪ!
ብቻ!
ለእውነት በእውነት ቆመሽ
ለፍትህ ለነፃነት ለህዝብ ብለሽ
ተናገሪ!
ወዳጅ እንዲሰማ አርገሽ
ተዋጊ!
ጠላት እንዲሰማው አርገሽ
አይደብርሽ ብእሬ
እቅጩን ሲጠይቁሽ
ሃይል ቃል ጨምሪበት
ምንአለበት
ለፍትህ ለነፃነት
መትከኔ ይታይበት
ንገሪው!
እስከሚገባው ድረስ
አልሰሜ ሁሉ እስኪሰማ
ያልነቃው ሁሉ እስኪነሳ
''ፎቼ ጉድ''
እንዲህ ኖሯል ወይ እስኪል
አርማውን እስኪያነሳ!
ንገሪው!
''ያኛውንም''
እጅ እጅ እስኪለው ድረስ
ባፍንጫው እስኪወጣ
ኢምንትነቱን እስኪያውቅ
መፈጠሩን እስኪጠላ
ከትግሉ መድረክ እስኪወጣ!
አወን! በይ ሂጂ ብእሬ አትፍሪ
ባሻሽ እንዳሻሽ አርገሽ
ለወደቁት ጓዶች ብለሽ
ስለ ፍትህ ስለእውነት
ያለሽን ተናገሪ

***

በይ ብእሬ
ማንን አትበይ
አወን...እሱን....ሰርጎ ገቡን
ያኔ ያንን ጓድ ስንቀብር
አርማውን አንስቻለሁ ያለውን
ከኛ ጋር ግራ እጁን አንስቶ
''እንበቀላለን'' የወጣውን
ኋላ ከቀብር ተመልሰን
ጓዶችን ለጠላት ሲያስማማ
እጅ ከፍንጅ የያዝነውን!
አወን ልክ ነሽ ብእሬ
እሱን....ሰርጎ ገቡን!
ዛሬ ደሞ ያች ጓዲት ሞታን
እንደገና ሰርጎን የገባውን

ጥንብ ያንሳውና
አርማውን
"እነሳለሁ" ነው?
ምናምን የወጣውን
እንደገና ከኛ ጋር
ግራ እጁን የቃጣውን
አወን ብእሬ ልክ ነሽ
እሱን...ሰርጎ ገቡን!
***
የቁን አትበይ ብእሬ....ሞልቷል
ያውልሽ ደግሞ ያኛውን
አወን ወዲያ "እነሱ" ጋር
ሹክክ ብሎ የቆመውን
ከሃዲውን!
ትላንት እኛ ስናጠቃ
ቀይ ሽብር ነኝ እያለ
"በስተግንባር" ተመስሎ
ያዙኝ ልቀቁኝ ያለውን
ዛሬ እኛ ስንጠቃ
በወዲያ በኩል የቆመውን
አወን ልክ ነሽ ብእሬ
እሱን ....ከሃዲውን
ጥቀሽለት
ያኔ ያ ከሃዲ ብእሩ
አዳልጦት የፃፈውን
አስታውሺው
ያኔ እዚያ አደባባይ ላይ
ስንፎክር
አብሮን የፎከረውን
ስንማማል
አብሮን ያስተጋባውን
አሳይው
ርቀቱን...ልዩነቱን
የዛሬውንና የትላንቱን
ክህደቱን
ከዚያማ ተይው ልቀቂው
ምን ቸገረሽ!?
አለ የጓዲቶች አጥንት
እሾህ ሆኖ ይወጋዋል
አለ የጓዶቻችን ደም
ጎርፍ ሆኖ ይወስደዋል
አለ የሰፊው ህዝብ ክንድ
ዶግ አመድ ያደርገዋል
አንቺ ብቻ
ጥቀሽ...አጣቅሺ...አመሳክሪ
ከልፈፋው እስከ ድርጊቱ ያለውን ተናገሪ
አመሳክሪ
የዛሬውን የትላንቱን ክህደቱን
አጋልጭው! አወን እሱን ከሃዲውን
****
የቁን አትበይ ብእሬ
እንዳፈር ነው
እሱን..
አጎንሽ..አፍንጫሽ ስር የቆመውን
ደፋሩን
ያን ሃቀኛ ጓዳችንን ደገፍ ብሎ የቆመውን
አወን እሱን
አስመሳዩን...አድርባዩን
በሃረግ ቅጥልጥል አስማት
በቃላት ድንፋታ ብርታት
"ዛሬም" እያለ
ዛር ያንደፋድፈውና
ዛሬም
"አለሁ" ብሎ ሊያስመስል
"ዛሬም"

እናንተ ጋ ነኝ ብሎ ሲምል
ግቢ ነፍስ ውጭ ሳይ ያለውን
አወን እሱን ብእሬ
አስመሳዩን አድር ባዩን!
አጋልጪ
ትላንት እንደዚያ የጠራ ሰው
ዛሬ ምላሱ ቢተሳሰር
''ከነሱ'' ሰፈር ቆሞ
''ግራ'' ቋንቋ ቢናገር
አጋልጪ! ምን አስፈራሽ ብእሬ?
ተርጉሚ ምላሱን እያፍታታሽ
ቋንቋውን እያጣራሽ
አዋርጂው!
ይቺቺ ክህደት....
ይቺቺ ቅጥፈት
ይቺቺ አድርባይነት እያልሽ
አናጥቢው
ያኔ ሌላ...አሁን ሌላ እያልሽ
አጋልጪ
እንቆቅልሹን ፍቺ
ልዩነቱን አመልክቺ!
አወን ብእሬ
እሱን ከጎንሽ የቆመውን
ያንን ጓዳችንን
ደገፍ ብሎ ያረፈውን
አወን ብእሬ
እሱን ደፋሩን አስመሳዩን አድርባዩን!
*****

እንዴት? አትበይ ብእሬ
እንዳሻሽ እንዳመቸሽ
ህቡእ ገብተሽ ይፋ ወጥተሽ
ሰማይ ወጥተሽ ምድር ገብተሽ
አይታክትሽ ብእሬ
ብቻ አስተምሪ አጋልጭ
አወን! አይታክትሽ ብእሬ
ሰርጎ ገቡን አናጥቢ
አስመሳዩን አንጓይ
ከሃዲውን አስተፊ
አወን አይታክችሽ ብእሬ
ግጠሚ አትቺ ተቺ
ተርቢ አሽሟጪ ተርቺ
ህቡእ ግቢ ይፋ ውጪ
ብቻ!
አስተምሪ አጋልጪ
ብቻ!
ፍትህ ነፃነት ሳልነው
የጓዶችን አርማ ሳነሳነው
ለአንዲት ኢትዮድያ ልጆች
ለዚች ምድር ታጋዮች
ብርሃን ጥራትን አምጪ!!!

ነገደ ጎበዜ
ኤደን / ደቡብ የመን/
ጥቅምት 1970 ዓ.ም.